# የዲሞክራሲያዊ ለዉጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ

## መተዳደሪያ ደንብ

### መግቢያ

ይህ የድጋፍ ድረጅት በፖለቲካ እንቅስቃሴዉ ሲደግፈዉ የነበረዉ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ በሃገር ዉስጥ እንዳይንቀሳቀስ በወያኔ መንግስት በመደረጉ ምክንያትና ከምርጫ 97 ጀምሮ ያለዉ የወቅቱ የፓለቲካ ሁኔታ ከበፊቱ በመቀየሩ የተነሳ ትግሉ፤ አደረጃጀቱ እንዲሁም የድርጅቱ ስም ካለዉ ነባራዊ ሁኒታ ጋር በተዛመደ መልኩ ማሻሻል አስፈሊጊ ሆኖ ተገኝተዋል።

ይህ የድጋፍ ድርጅት አሁንም ቅንጀት ይዞት የተነሳዉን ራእይ ላይ በመመርኮዝና በመፅናት የዜጎች እኩልነት፣ ነፃነትና ሰብአዊ መብቶች የሚከበርበትና ሕዝብ የስልጣን ባለቤት የሚሆንበት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት ቅድሚያ የሚሰጠዉ አብይ ጉዳይ መሆኑን ያምናል:: የኢትዮጵያ ህዝብ አምባገነናዊ ስርዓትን በማስወገድ ፍትህ፣ እኩልነትና ዱሞክራሲ የሰፈነበት ስርዐትን ለማስፈንና ለመገንባት የሚያደርገዉን ትግል በታማኝነትና በቁርተኝነት ይታገላል።

የዲሞክራሲያዊ ለዉጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ ከለይ የተዘረዘሩትን ሁኒታዎች የሚያማሉና በጠቅላላ ጉባኤዉ አብዛኛ ድምጽ የተደገፉ፤ በብሄራዊ አንድነትና በመድብለ ፓርቲ የሚያምኑ፣ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ አሰራር የሚከተሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይደግፋል።በዚህም መሰረት በአሁኑ ወቅት የአርበኞች ግንቦት7 ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ እና ሰማያዊ ፓርቲን ይደግፋል።

በተጨማሪ ሌላ ድርጅት ወደ ፊት በጠቅላላ ጉባኤዉ ዉሳኔ ሊካተቱ ይችላሉ።ሆኖም ይህ ደንብ ስራ ላይ በዋለበት ወቅት ድጋፍ የሚደረግላቸዉ ድርጅቶችም ሆኑ ወደ ፊት የሚካተቱት በጠቅላላ ጉባኤዉ ግምገማ ዉሳኔ የድጋፍ አጋርነታቸዉ ሊቋረጥ ይችላል።

በኖርዌይ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያ ወዳጆች፤ የፖለቲካና የሲቢክ ማህበራት ለተጀመረዉ የዲሞኪራሲ ትግል የተቻላቸዉን እንዲያበረክቱ የድጋፍ ድርጅቱ ያስትባብራል በጋራም ይሰራል፤ ለዚህና መሰል መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዉ ያመች ዘንድ ድጋፍ ድርጅቱ በራሱ የቆመ፣ማንም የማያዘዉ ነጻ ድርጅታዊ መዋቅር ያለዉ ሆኖ እንዲዋቀር ተደርጓል።

እንዲሁም አገር ቤት የነበረዉ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ህጋዊ ስሙንና ምልክቱ በወያኔ መንግስት በመነጠቁ የተነሳ ምክንያት የቅንጅት የድጋፍና የዕድገት ድርጅት በኖርዌይ ተብሎ የሚጠራዉ በአዲስ መጠሪያ ማለትም፤ ዲሞክሪሲያዊ ልዉጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌ በሚል እንድተካ ተደርጓል;;

ስለሆነም የድጋፍ ድርጅቱ የሚያካሂደዉን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሥርዓት ባለዉ መንገድ ለማካሄድ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለዉ አሰራር እንድኖር፣የዴርጅቱን አጠቃላይ የሥራ መስኮች፣የአሰራር መዋቅሮች፣ስሌቶችና አቅጣጫዋች በማሳያት፣የአባላትን የስራ ድርሻና የሥራ ግንኙነት መወሰን እንዲቻል ባለፉት ዓመታት ሲሰራበት የነበረዉ የዉስጥ ደንብ ከዚህ በታች በቀረበዉና 5 ምዕራፎችንና 33 አንቀጾችን ባካተተዉ ድንጋጌ ተተክቷል።

# ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ዉስጥ ድሞክራሲያዊ ለዉጥ ለማምጣት ድጋፍ ለመስጠት የተቋቋመ የዲሞክሪሲያዊ ለዉጥ በኢት ዮጵያ ድጋፍ ድርጅት በኖርዌይ መተዳደሪያ ደንብ ተብል ሊጠቀስ ይችላል;;

**አንቀጽ 2 የድርጅቱ ስም**

የድርጅቱ መጠሪያ ስም ዲሞክሪሲያዊ ለዉጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ ነዉ።

**አንቀጽ 3 የድርጅቱ ጽ/ቤት**

የድጋፍ ድርጅቱ ጽ/ቤት ኦስሎ ከተማ ነዉ ፤እንዳአስፈሊጊነቱ በጠቅላላ ጉባኤዉ ዉሳኔ መሰረት በኖርዌ ሊላ ከተማ ሊሆ ይችላል።

**አንቀጽ 4 ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከኦስሎ ከተማ ዉጪ በሊሎች ከተሞች በጠቅላላ ጉባኤዉ ዉሳኔ መሰረት ሊቋቋሙ ይችላሉ።

ይኸን መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ አመራር አመራረጥና ዝርዝር የአሰራር ሁኔታ ከዋናዉ የድጋፍ ድርጅት ስራ አስፈፃሚ ከሚቴ በሚወጣ መመሪያ ይሆናል።

**አንቀጽ 5 አርማ**

የዲሞክሪሲያዊ ለዉጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ የራሱ የሆነ አርማ ይኖረዋል።

**አንቀጽ 6 የድርጅቱ ዓላማ**

በአገራችን ኢትዮጵያ ሕዝባዊ መንግስት ለመመስረት፣ዱሞክራሲያዊ ስርአት ለማስፈንና የህግ የበላይነትን እዉን ለማድረግ ለሚታገሉ ድርጅቶች የፖለቲካ፣የኢኮነሚና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን መስጠት ነዉ;;

**አንቀጽ 7 የድርጅቱ ተግባር**

7.1. የሚድገፉ ድርጅቶችን ዓላማ ፣ፕሮግራምና እንቅስቃሴ ማስተዋወቅ

7.2. ለሚደገፉ ድርጅቶች አስፈላጊዉን ድጋፍ መስጠት

7.3. ሰላማዊ ሰልፎችን፣ የተለያዩ የተቃዉሞና የድጋፍ ትዕይንቶችን በማድረግ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚደረገዉን የሰብአዊ መብት ረገጣ መቃወምና ማጋለጥ

7.4. ሕዝባዊ ስብሰባዋችን፣ሰሚናሮችንና ሲምፖዚየሞችን በማዘጋጀት የህዝብን ግንዛቤና ንቃት ማዳበር

7.5. ከኖርዌይ መንግስት ባለስልጣናት ፣የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች የሙያ ማህበራትና ታዋቂ ግለሰቦች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የድፕሎማሲ ሥራ ማካናወን፣

7.6. በኖርዌና በሊሎች አገሮች ካሉ ኢጋር የፖለቲካ ድርጅቶች፣የድጋፍ ድርጅቶች፣መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በኢትዮጵያ ድሞክራሲያዊ ለዉጥ ልይ በጋራ በመስራት ትብብር ማዴረግ፣

7.7. በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መግለጫ መስጠት፣

7.8. ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ለድርጅቱና ለሚደገፉ ድርጅቶች ማሰባሰብ፣

7.9. ለሚደገፉ ድርጅቶች ጠቃሚ ሀሳቦችን ማቅረብና ልጥንካሬ የሚበጁ አስተያየቶችን መስጠት

7.10. ከሚደገፉ ድርጅቶች ዋና ፅ/ቤቶች የሚተልለፉ ሊሎች ተግባራትን ማከናወን፣

## ምዕራፍ 2

**ድርጅታዊ መዋቅር**

ዲሞክሪሲያዊ ለዉጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ ጠቅላላ ጉባኤ; የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣የተለያዩ ንኡስ ኮሚቴዎችንና ኦዲትና እንስቲክሽንን ያካተተ ድርጅታዊ መዋቅር ይኖረዋል;;

**አንቀጽ 8 ጠቅላላ ጉባኤ**

**አንቀጽ 9 የጠቅላላ ጉባኤዉ ስልጣንና ተግባር**

9.1. ጠቅላላ ጉባኤዉ የድጋፍ ድርጅቱ ፍተኛ የአመራር አካል ነው

9.2. የድጋፍ ድርጅቱን መተድደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የሥራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ አጠቃላይ መመሪያዎችን ይሰጣል

9.3. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴንና የኦዲት ኮሚቴን ይመርጣል

9.4. በአመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ፡ የሚደግፋቸውን ድርጅቶች በአመት ሁለቴ ይገመግማል።

9.5. አስቸከኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም የሥራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ ወይም የአባልነት ግዴታቸዉን በሚወጡ በሁለት ሦስተኛዉ የአባላት ጥያቄ ልዩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል

9.6. ከስራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ፤ ከኦዲትና እንስፔክሽን ኮሚቴ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን መርምሮ በማፅደቅ በሥራ ሊይ እንዲዉል ያደርጋል

**አንቀጽ 10 የጠቅላላ ጉባኤዉ የምርጫ አመራርጥ ሥርዐት**

የስራ አስፈፃሚና የኦዲት ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚመረጡ ሲሆን አመራረጣቸዉም እንደሚከተለዉ ይሆናል

10.1. አንድ ሰብሳቢና ሁለት አባላት ያካተተ ሦስት አባላት የሚገኙበት አስመራጭ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤዉ በእለቱ ይመረጣል

10.2. በድርጅቱ አሰራር መሰረት አባልነታቸዉ የፀደቀላቸዉ በስብሰባዉ የተገኙ አባላት በዕጩነት መቅረብ ይችላሉ

10.3. ለቀጣይ ሥራ እንዲያመች ከቀድሞዉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤዉ ያመነባቸዉን ከአራት ያልበለጡ አባላት ሊመረጡ ይችላሉ.

10.4. ለሁለም የሥራ ክፍሎች በሚቀርቡት እጩዎች ላይ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት በሚስጥር ይሆናል

10.5. ከቀረቡት እጩ አባላት መካከል ከፍተኛ የድምፅ ብልጫ በማግኘት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት የተመረጡትን አባላት የአስመራጭ ኮሚቴዉ ሰብሳቢ ለጉባኤዉ ያሳዉቃል

10.6. ከተመረጡ የስራ አስፈፃሚ አባላት መካከል በተለያየ ምክንያት አባል ሲጎል ስራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ ለጠቅላላዉ ጉባኤ አቅርቦ ያስመርጣል

**አንቀጽ 11 የጠቅላላ ጉባኤዉ የዉሳኔ ድምፅ አሰጣጥ**

11.1. የአባልነት ግዴታቸዉን ከሚወጡ ከጠቅላላ አባላት ወይም አስሎ ከተማ ከሚኖሩ የድርጅቱ አባላት መካከሌ ሁለት ሦስተኛዉ በስብሰባዉ ከተገኘ ምልአተ-ጉባኤዉ እንደተሟላ ይቆጠራል

11.2. ለሁለት ተከታታይ ጊዜዎች በምልዓተ ጉባኤ አለመሟላት የተነሳ በጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ ለመስጠት ካልተቻለ ለሦስተኛ ጊዜ ስብሰባ ተጠርቶ በተገኘዉ አባላት ብቻ ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ ይቻላል

11.3 ማናቸዉም ዉሳኔዎች የሚተሊለፉት በስብሰባዉ በተገኙ አባሊት አብላጫ ድምፅ ይሆናል

11.4. ዉሳኔዉ እኩል ድምፅ ካገኘ ሊቀመንበሩ ያለበት ያልፋል

**አንቀጽ 12 ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**

ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ስምንት አባላት ይኖሩታል;;

**አንቀጽ 13 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር**

13.1. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከጠቅላላ ጉባኤዉ ቀጥሎ የዴርጅቱ ከፍተኛ አመራር አካል ነዉ.

13.2. በወር ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል

13.3. የድርጅቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ያስተባብራል፣አመራር ይሰጣል

13.4. የድርጅቱን ገንዘብ፣ንብረትና በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ያዉላል

13.5. በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚፀድቁትን መመሪያዎችና ሊሎች ዉሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል

13.6. በድርጅቱ ዉስጥ የሥርዓት ጉድለት ሲኖር በህጉ መሰረት አስፈሊጊዉን እርምጃ ወስዶ ለጠቅላላ ጉባኤዉ ያሳዉቃል

13.7. ከመሰልና አቻ የድጋፍና የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የትግል ግንኙነት ያደርጋል

13.8. የድርጅቱን ፅ/ቤት አስተዳደር በተመለከተ መመሪያ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል

13.9. ለጠቅላላ ጉባኤዉ የሥራ ክንዉን ሪፖርት ያቀርባል

13.10. የሥራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ ዕድሜ ሁለት ዓመት ብቻ ነዉ

13.11. የድርጅቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤዉ ይሆናል

13.12. ይህ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት የሥራ ዘርፎች ይኖሩታል

ሀ. ሊቀመንበር

ለ. ም/ሊቀመንበር

ሐ. ዋና ፀሐፊ

መ. ድርጅት ጉዳይ

ሰ. ሕዝብ ግንኙነት

ረ. የሎቢና ዲፕሎማሲ ዘርፍ፡

ሸ. ሂሳብ ሹም

ቀ. ገንዘብ ያዥ

**አንቀጽ 14 ሊቀመንበር**

14.1. የድርጅቱን የዕለት ተዕለት ተግባራት ያከናዉናል፣ድርጅቱን ይመራል

14.2. ድርጅቱን በማናቸዉም መድረክ ይወክላል፣ድርጅቱን በሚመለከት መግለጫ ይሰጣል

14.3. ከጠቅላላ ጉባኤዉና ከሥራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ የሚተላለፉ ዉሳኔዎችንና የሚሰጡትን ሥራዎች በስራ ላይ ያዉላል

14.4. በድርጅቱ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር መሠረት ወጭዎችን ያዝዛል

14.5. ወጪ ደብዲቤዎችንና የተለያዩ ሰነዶችን ይፈርማል

14.6. ከፀሐፊዉ ጋር በመመካከር በፀሐፊዉ በኩል ስብሰባ ይጠራል

**አንቀጽ 15 ም/ ሊቀመንበር**

15.1. ሊቀመንበሩ በሌለበት ተክቶ ይሰራል.

15.2. የመወያያ እርሶችን በማዘጋጀት በንድፈ ሀሳቦች ላይ አባላትን ያወያያል፣

15.3. የዴርጅቱን ዴከመትና ጥንካሬ እየገመገመ ሆችግሮች መፍትሄ ይፈሌጋሌ፣

15.4 የሥራ ጫና የበዛባቸዉን ክፍሎች ያግዛል፣

15.5. ከገንዘብ ያዡ ጋር በመሆን የዴርጅቱን ሂሳብ በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳሌ.

15.6 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሊሎች ተግባሮች ያከናዉናል

**አንቀጽ 16 ዋና ፀሐፊ**

16.1. የስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣የተያዘዉንም ቃለጉባኤ በሚቀጥለዉ ስብሰባ ቀን የዉይይት አጀንዳ ከመከፈቱ በፊት ለስራ አስፈፃሚ አቅርቦ ትክክለኛነቱን እንዲረጋገጥ የደርጋል፣

16.2. ከተለያዩ ኮሚቴ ሃላፊዎች የሚደርሱትን ጉዳዮች አቀናብሮ ለሊቀመንበሩና ለስራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ ለዉሳኔ ያቀርባል፣ዉሳኔዎችንም ለሚመለከታቸዉ ያሰራጫል

16.3. ከሊቀመንበሩ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣አጀንዳዉን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በቅድሚያ ይልካል፣ስብሰባም ይጠራል

16.4. የድርጅቱ ፅ/ቤት አስተዳደር በቅልጥፍና እንዲካሄድና መዛግብት በስርአት እንዲያዙ ያደርጋል፣

16.5. በየሦስት ወር የሚዘጋጀዉን የድርጅቱን የሥራ ሪፖርት አቀናጅቶ ያዘጋጃል፣ለሥራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ ሪፖርቱን ለሚመለከታቸዉ ያሰራጫል

16.6. የድርጅቱን ሰነዶችና ማህተም ይይዛል፣ይጠብቃል

16.7. በቃለጉባኤዉ መሰረት ሥራዎች መሰራታቸዉን ይከታተላል

**አንቀጽ 17 የድርጅት ጉዳይ ዘርፍ**

ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚተላለፉትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናል

17.1. የድርጅት አባላትን ይመለምላል፣ይመዘግባል፣ያደራጃል

17.2. የተመለመሉ አባላትን ለሙሉ አባልነት ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣የድርጅቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከተቀበለዉ በሙሉ አባልነት ይመዘግባል፣

17.3. የድርጅቱን ንዑስ ቅርንጫፎች በየክፍለ ሀገራት ያቋቁማል፣ያደራጃል፣እድገታቸዉን ይከታተላል

17.4. አባላት ለዴርጅቱ አላማና ዲሲፕሊን ተገዢ እንዲሆኑ ይከታተላል፣ይቆጣጠራል

17.5. የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ ከስራ አስፈፃሚዉ በሚሰጠዉ መመሪያ መሰረት አጣምሮ ይሰራል፣ራሳቸዉን ችለዉ የሚዋቀሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል

17.6. የሙሉና ያእጩ አባላትን ዝርዝር በመለየት በየወቅቱ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያሳዉቃል

17.7. አባላት የተጠናከረ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያጠናል፣ለችግሮች መፍትሄ ይፈልጋል

17.8. የዘርፉን ንዐስ ኮሚቴ የሥራ መመሪያ ያዘጋጃል

17.9. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሊሎች ተግባሮች ያከናዉናል

**አንቀጽ 18 የሎቢና ዲፕሎማሲ ዘርፍ**

ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚተላለፉትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ተግብራት ያከናዉናል

18.1. በኖርዌይ ከሚገኙ መሰል ዓላማ ካላቸዉ ድርጅቶች ጋር ጤናማ የትግል ግንኙነት እንዲኖር በማቀድ ይሰራል

18.2. ከመንግስት ባለስልጣናት፣መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች፣ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የድርጅቱን ዓላማ ያራምዳል፣ለስምምነት የሚያበቁ ተግባሮችን ያስፈፅማል፣ በአጠቃሊይ በኖርዌይ እና ከኖርዌይ ዉጪ ባሉ አገሮች የሎቢና ዲፕሎማሲ ስራዎችን ይሠራል

18.3. የሚደግፉና ሊደገፍ የሚገባ የፖለቲካ ደርጅቶችን የአገር ዉስጥ እና ከአገር ዉጭ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እየገመገመ በየስድስት ወሩ ለዉይይት ያቀርባል

18.4. ድርጅቱ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ዕርዳታ የሚያገኝበትን መንገድ ያጠናል፣ ለተግባራዊነቱ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ይወያይበታል፣

18.5. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ የሚሰጡትን ሊሎች ተግባረት ያከናዉናል

**አንቀጽ 19 የሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ**

ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ የሚተላለፉትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናል

19.1. የድርጅቱን ዓላማና የሚያከናዉናቸዉን ልዩ ልዩ ተግባራት ያስተዋዉቃል

19.2. ድርጅቱ የሚያካሂዳቸዉን ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ ሠላማዊ ሰልፎች፣ የአዉደ ጥናት ዝግጅቶችና ጋዜጣዊ መግለጫዎችን በሃላፊነት የስተባብራል፣ይመራል

19.3. የደርጅቱን ፕሬስ ዉጤቶች ለህዝብ ያሰራጫል፣ ድጋፍ የሚሰጣቸዉን ድርጅቶች የድህረ -ገፅ እንቅስቃሴ ለህዝብ ያስተዋዉቃል

19.4. ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳን የሚመለከቱ እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፣ በድርጅቱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አፅድቆ ተግባራዊ ያደርጋል

19.5. የድርጅቱ ቃል አቀባይ ሆኖ ይሰራል

19.6. ለተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ከፖሊስ ፍቃድ ይጠይቃል

19.7. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሊሎች ተግባራት ያከናዉናል

**አንቀጽ 20 የፋይናንስ ጉዳይ ዘርፍ**

ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ የሚተላለፉ መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናል

20.1. የድርጅቱ የሒሳብ ስራ ዘመናዊና ሥርዓት በጠበቀ መንገድ መካሄዱንና ትክክለኛነቱን ይቆጣጠራል

20.2. ለሒሳብ ሥራ አስፈሊጊ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ ይይዛል፣ ይቆጣጠራል

20.3. በየወቅቱ የሂሳብ ሪፖርት እያዘጋጀ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያሳዉቃል፣ ዓመታዊ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤዉ ያቀርባል

20.4. ከገንዘብ ያዡ ጋር በመሆን ገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ይተልማል ወደ ድርጊት የሚተረጎምበትን መንገድ ይቀይሳል

20.5. የደርጅቱን በጀት ከገንዘብ ያዡ ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያፀድቃል

20.7. ለደረሰኞች ማረጋገጫ የሚውል ማህተም ይይዛል፣ ይጠብቃል

20.8. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሊሎች ተግባባራተ ያከናዉናል

**አንቀጽ 21 የድርጅቱ ገንዘብ ያዥ**

21.1. የተጠናከረ የወርሃዊ መዋጮ አሰባሰብ ዘዴ እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፣ የደርጅቱ አባላአትና ደጋፊዎች ወርሃዊ መዋጭዎችን በትክክል መክፈላቸዉን ከድርጅት ጉዳይ ዘርፍ ጋር በመሆን ይከታተላል

21.2. የድርጅቱን ገንዘብ ሥርዓት ባለዉ መንገድ ይይዛል፣ ከክፍለ ሃገሮች; በተለያዩ ኮሚቴዎችና ከተለያዩ ዝግጅቶች የሚሰበሰበዉን ገንዘብ ተከታትሎ ገቢ ያደርጋል

21.3. 1500 ክሮነር ፔቲ ካሽ ባእጁ ይይዛል፤ የሚንቀሳቀሰዉም በወጪ ማዘዣ ሆኖ ማዘዣዉ ሦስት ኮፒ ይኖረዋል፣አንድ ኮፒ ለሂሳብ ሹም ይሰጣል

21.4. የድርጅቱ የፋይናንስ እንቅስቃሴ በዓመታዊ የኦዲት ምርመራ እንዲረጋገጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል

21.5. የገቢና ወጪ ደረሰኞች የሂሳብ መጠቀሚያ ሰነዶች በየወቅቱ ከሂሳብ ሹሙ እየፈረመ ይረከባል

21.6. የባንክ ሒሳብ እንቅሳቃሴን ይከታተላል፣ ሰነዶችን በተገቢ መንገድ ይይዛል

21.7. ከፋይናንስ ሃላፊዉ ጋር በመሆን ገቢ ማስገኛዎችን ይቀይሳል፣ ወደ ድርጊት የሚተረጎሙበትን መንገድ ያመቻቻል

21.8. ከም/ሊቀመንበሩ ጋር በመሆን የድርጅቱን ሂሳብ በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል

21.9. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል

**አንቀጽ 22 ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተላቸዉ የአሠራር ስልቶች**

22.1. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለዉሳኔ በቀረቡ ነጥቦች ዙሪያ በቂ ዉይይት ከአደረገ በኋላ ዉሳኔዉን የሚሰጠዉ በተቻለ መጠን ሁሉም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እንዲስማሙበት ጥረት ያደርጋል፣ ከበቂ ጥረት በኋላ ዉሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይወሰዳሉ

22.2. የድጋፍ ድርጅቱም ሆነ ድጋፍ የሚሰጣቸዉ ፖለቲካ ድርጅቶች በአገር ቤትም ሆነ ካገር ዉጪ የሚያደርጓቸዉን ለህብረተሰቡ ይፋ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችንም ሆነ መግለጫዎች ለአባላትም ሆነ ለደጋፊዎች እንዱሁም ለሕብረተሰቡ የሚነገሩት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ በተስማማበት ሁኔታና ጊዜ ብቻ ይሆናል

22.3. በክፍል ሃላፊዎች በጋራ የተወሰኑ ዉሳኔዎችን ለማስፈፀም በየስራቸዉ ከአባላትና ከደጋፊዎች የተዉጣጡ ንዐስ-ኮሚቴዎችን አደራጅተዉ ይሠራሉ;; የየክፍሉ ሃላፊዎች በንዐስ-ኮሚቴዉ የሚሰሩትን የንዐስ-ኮሚቴ አባላትን

ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርበዉ ያፀድቃሉ፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ አንድ የንዑስ-ኮሚቴ አባልን ሊቀበል ወይም ላይቀበል ይችላል

**አንቀጽ 23 ኦዲትና ኢንስፒክሽን**

23.1. የድርጅቱ የሂሳብ መዝገብ አያያዝና አሠራር ደንብን የተከተለና ለብክነት ያልተጋለጠ መሆኑን ይከታተል፣ ይቆጣጠራል፣ጥፋት ተስርቶ ሲገኝ የእርማት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል

23.2. የድርጅቱ የፋይናንስ ሪፖርት ትክክል መሆኑን አጣርቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉና ለጠቅላላ ጉባኤ በፅሁፍ ሪፖርት ያቀርባል

23.3. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ንዑሳን ኮሚቴዎችና ባጠቃላይ የድርጅቱ እንቅስቃሴ ከህግ አንፃር መሰራቱን ይቆጣጠራል፣እርምት ይሰጣል፣ለጠቅላላ ጉባኤዉ ሪፖርት ያቀርባል

## ምዕራፍ 3

**አንቀጽ 24 አባልነት**

24.1. ማንኛዉም የድርጅቱን ዓላማና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለና እድሜዉ ከ 18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ወዳጅ በአባልነት ሊመዘገብ ይችላል

24.2. ምዝገባዉን ካጠናቀቀ ከሦስት ወር በኋላ ከእጩ አባልነት ወደ ሙሉ አባልነት ሊዛወር ይችላል

24.3. አንድ እጩ አባል መምረጥም ሆነ መመረጥ አይችልም፣

24.5 ከሚደግፋቸዉ ድርጅቶች በሐገር ቤትም ሆነ በዉጭ ሃገር አባል የነበረ ሰዉ የአባልነት ጥያቄ ሲያቀርብ በቀጥታ በአባልነት ይመዘገባት፣

**አንቀጽ 25 የአባላት መብቶች**

25.1. ማንኛዉም በድጋፍ ድርጅቱ አባልነት የተመዘገበና ግዴታዉን ያሟላ አባል የመምረጥና የመመረጥ መብት አለዉ

25.2. ማንኛዉም አባል ድርጅቱ በሚያዘጋጀዉ የአባላት ስብሰባ ላይ የመሳተፍ፣ ሀሳብ የመስጠት፣ የመጠየቅና የመተቸት መብት አለዉ

25.3. ማንኛዉም አባል የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ፣ አሰራርና ስልት፤ የድርጅቱን ዉስጣዊ ጉዳዮች የመተቸትና ሊላ አማራጭ ሃሳብ የመስጠት መብት አለዉ

25.4. ማንኛዉም አባል የድርጅቱን የ6 ወር የስራ እንቅስቃሴና ክንዉን ሪፖርት የማወቅ መብት አለዉ

25.5. ሊሎች የአባላት መብቶች እንደየሁኔታዉ በአባላት ድምፅ ብልጫ ይወሰናሉ

**አንቀጽ 26 የአባላት ግዴታዎች**

26.1. ማንኛዉም አባል የሚፈለግበትን የአባልንት ወርሃዊ መዋጮና ሊሎች ክፍያዎችን የመፈፀም ግዴታ አለበት

1.1 የመኖሪያ ፈቃድ ያለው፡ ስራ የሚሰራ/ ገቢ ያለው ማንኛውም አባል በወር 100 ክሮነር የአባልነት መዋጮ ይከፍላል

1.2 በመጠለያ ካምፕ የሚኖር/የምትኖር ማንኛውም አባል በዓመት 300 ክሮነር የአባልነት መዋጮ ይከፍላል

1.3 ከላይ ከተጠቀሱት ምድብ የማይጠቃለል አባል የሰራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተነጋግሮ ውሳኔ ይሰጥበታል

26.2. የደርጅቱን አሊማዎችና ስራዎች ለሕዝብ ማስተዎወቅ

26.3. የድርጅቱን የአሰራር ሚስጥርና ዲስፐሊን የማክበርና ድርጅቱን ከሚጎዱ ድርጊቶች መታቀብ

26.4. ከድርጅቱ ለሚላኩ የኢሜሌና ሊሎች መልዕክቶች በወቅቱ መልስ መስጠት

26.5. ከድርጅቱ የሚሰጡትን ሊሎች ሃላፊነቶች በወቅቱ መወጣት

26.6. ወቅታዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ገንዘብ ማስገኛ መንገዶችን፣ አባልና ደጋፊ ማብዣና መቀስቀሻ ስሌቶችን ማመንጨት

26.7. ሊሎች ግዲታዎች እንደየሁኔታዉ በአባላት ድምፅ ብልጫ ይወሰናሉ

**አንቀጽ 27 አባልነት ስለመቋረጥ**

27.1. አባሉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ

27.2. አባሉ በራሱ ፍቃድ የመልቀቂያ ደብዳቤ ሲያቀርብ

27.3. አባሉ በአንቀጽ 28 መሰረት የዴስፐሊን እርምጃ ሲወሰድበት

**አንቀጽ 28 የዲሲፐሊንና ሥነስርዓት እርምጃ አወሳሰድ**

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አንድን አባል ለጊዜዉ ከአባልነት አግዶ ሙሉ በሙሉ ከአባልነቱ እንዲሰረዝ ለጠቅላላ ጉባኤ ለማፀደቅ የሚያቀርበዉ ከሚከተለት አንዱ ሁኔታ ሲሟላ ነዉ፣

28.1. የድርጅቱን ሚስጥር ሲያባክን፣ድርጅቱን ለማዳከም ሲጥር ከተገኘ

28.2. በድርጅቱ ዉስጥ ክፍፍል ለማድረግ ሲጥር ከተገኘ

28.3. ያለበቂ ምክንያት ለስደስት ተከታታይ ወራት ወርሃዊ መዋጮዉን ያቋረጠ

28.4. የድርጅቱን ገንዘብና ንብረት የወሰደ ወይም እምነት አጉሎ የተገኘ፣ በተረጋገጠ ማስረጃ በህግም ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል

## ምዕራፍ 4

**የድርጅቱ ገቢና ንብረት አያያዝ**

**አንቀድ 29 የገቢ ምንጮች**

29.1. ከአባላት የሚሰበሰብ የአባልነት መዋጮ/100 ክሮነር ወርሃዊ መዋጮ/

29.2. ከአባላትና ከደጋፊዎች በፈቃደኝነት የሚሰበሰብ ድጎማ

29.3. በተለያዩ ዘዴዎችና ወቅቶች ከሚደረጉ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች የሚገኝ ገቢ

29.4. ከተለያዩ ምንጮች የሚገኝ የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ስጦታዎች

**አንቀጽ 30 የድርጅቱ የንብረትና የገንዘብ አስተዳደር**

30.1. በድርጅቱ የሚሰበሰብ ማንኛዉም ገንዘብ በዲሞክራሲያዊ ለዉጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ይሆናል

30.2. ማንኛዉም በልገሳ ወይም ከአባላት መዋጮ የሚገኝ ገንዘብ በህጋዊ ደረሰኝ ይስበሰባል በድርጅቱ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ይሆናል

30.3. የደርጅቱ ንብረቶች በሥርዓት ተመዝግበዉ በፋይናንስ ጉዳይ ሃላፊዉ ሥር ይቀመጣሉ

30.4. የፋይናንስ ክፍል ሃላፊ እስከ 1500/አንዴ ሺህ አምስት መቶ/ክሮነር ድረስ ወጪ ማድረግ ይችላል

30.5. የድርጅቱ ሊቀመንበር እስከ 5000/አምስት ሺህ/ክሮነር ዴረስ ወጪ ማዘዝ ይችላል

30.6. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ እስከ 15000/አስራ አምስት ሺህ/ክሮነር ድረስ ወጪ ማዘዝ ይችላል

30.7. ከአስራ አምስት ሺህ/15000/ክሮነር በላይ የሆኑ ወጪዎች በጠቅላላ ጉባኤ መወሰን መጽደቅ ይኖርባቸዋል

## ምዕራፍ 5

**አንቀጽ 3 ደንቡን ስለማሻሻል**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከጠቅላላ አባላት ሁለት ሦስተኛዉ በሚያቀርበዉ ጥያቄ ወይም የሥራ አስፈፃሚዉ ኮሚቴ በሚያቀርበዉ ሁሳብ መሰረት እንደሁኔታዉ ሊሻሻል ይችላል።

**አንቀጽ 32 ድርጅቱን ስለማፍረስ**

የደጋፍ ደርጅቱ የሚፈርሰዉ በጠቅላላዉ ጉባኤ ዉሳኔ ነዉ።

**አንቀጽ 33 ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ተሻሽሎ የተቀረጸዉ መተዳደሪያ ደንብ ከ----- ቀን---- እንደ ኤሮፓዊያን ዘመን አቆጣጠር ጀምሮ የፀና ይሆናል።